
ولكن ليطمئن قلبي
ልቤም እንዲረጋጋ
مَعاً ضد الإلحاد
ፈጣሪን የሚክዱትን
በጋራ እንከላከል
2
ماتَ الصَّغيرُ فحزنَ القلبُ الكبيرُ..
وكسفَتِ الشَّمسُ
ትንሹ ሞተ የትልቁም ልቡ አዘነ
ፀሐይዋም ተጋረደች
( تَوافُقٌ زَمَنيٌّ احتاجَ إلى بَيانٍ
صَريحٍ وتَوضيحٍ صارِمٍ)
(በጊዜ መገጣጠም
ማብራሪያና ገለጻ
እፈልጋለሁ)
ድርሰት - ሐሰን ሺባኒ
تأليف: حسن شبّاني
ትርጉም - ሰይፈዲን አበሻ ያሲን
دار إتقان للنشر والتوزيع
جمعية إعرف النبي محمد
1/16

# ፈጣሪን የሚክዱትን በጋራ እንከላከል

# معاً ضد الإلحادِ 2

## ምክንያቱም ልቤ እንዲረጋጋ ነው

## ولكنْ ليطمئنَّ قلبي

## ትንሹ ሞተ የትልቁም ልብ አዘነ
## ፀሐይዋ ተጋረደች

مَاتَ الصَّغيرُ فحزِنَ القلبُ الكبيرُ ..

وكسفَت الشَّمسُ

( تَوافُقٌ زَمَنيٌّ احتاجَ إلى بَيانٍ صَريحٍ وتَوضيحٍ صارِمٍ)

(በጊዜ መገጣጠም ማብራሪያና ገለጻ እፈልጋለሁ)


تأليف: حسن شبّاني

ድርሰት – ሐሰን ሺባኒ



جمعيۃ اِعرف النبي محمد ﷺ دار إتقان للنشر والتوزيع



ትርጉም: ሰይፈዲን አበሻ ያሲን



ዳረል ኢትቃን የኢስላም መልእክቶች ሕትመትና ስርጭት ክፍል

الطبعۃ الأولى 2022

ሁለተኛ እትም 2022 ዓ. ል.



جميع الحقوق محفوظۃ للمؤلف. يُمنع نسخ أو طباعۃ أو تخزين أو إعادة إنتاج هذا الكتاب أو أي جزء منه بكل طرق الطبع والتصوير والوسائط الالكترونيۃ والميكانيكيۃ.



http: //Knowprophetmohammad.com

info@knowprophetmohammad.com

## ይህ መፅሐፍ መታሰቢያነቱ

ይህን መልክት ሳዘጋጅ ልዩ ኩራትና ኋይል ይሰማኛል፤ እንዴትስ አይሰማኝም ? የነብይነትን ትልቁን ደረጃ የተጎናፀፉትና የነብያቶች መጨረሻ ነብይ (ዓለይሂ ሰላት ወሰላም) መልእክት (ከከሃዲያን ጥቃት ለመከላከል ብዕሬን አነሳለሁ)።

በወጣትነት ዘመኔ ታሪኬ የነበረው፤ ሰከንደሪ እያለሁ የመጀመርያ አመት ላይ የልብወለድ ፁሑፎችን በማዘጋጀት ስወዳደር፤ በልብወለድ ፁሑፍ ውድድር አንደኛ በመውጣት አሸናፊ ሆኛለሁ፤ ቀስ በቀስም ይህ ታሪኬ ተረሳ፤ የሸሪዓን ትምህርት በመማርና በማስተማር ከንፁሕ ልቦች (ከተማሪዎች ጋር) በሥራ ተወጠርኩ፤ ከዚያም የመስጊድ ኢማምና ኸጢብ በመሆን አገልግዬ፤ የአስተማሪነቴን፤ የኢማምነቴንና ከዚያም በፊት የአባቴን ተሞክሮ በማከል፤ በቤተሰብ ዙሪያ የምክክር ዘርፍ ጠልቄ በመግባት ተሳትፊያለሁ።

ይኸው አሁን እኔ ተከታታይ የሆኑ ተሞክሮዎቼን በመጭመቅ፤ ታዳጊ የሆኑ ወጣት ወንዶችንና ወጣት ሴቶችን በማሰባሰብ፤ የአዋቂዎችና የአዛውንቶች ልብ የማይዋጥላቸውን ጉዳይ፤ ምናልባት ለወጣቶቹ ልቦች እንዲዋጥላቸው ለማድረግ ተነስቻለሁ።

ይህንንም መፅሐፍ መታሰቢያነቱ፡- የነብዩን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ፍቅር ላስተማረኝ አባቴ አላህ ይማረውና፤ በተጨማሪ በአስቸጋሪ ወቅት ላይ ብሩሕ ተስፋ በማመላከት ላስተማረችኝ እናቴ፤ እና የሕይወት ውጣ ውረዶችን ተሸክማ ከጎኔ ለቆመችው ባለቤቴ፤ እነሱንም እየታገስኩ፤ እነሱም እየታገሱኝ፤ የአባትነት ትርጉሙን ለተማርኩባቸው ልጆቼ እንዲሆን አድርጌዋለሁ።

በመጨረሻም የዳረል ኢትቃን የሕትመትና የሥርጭት ክፍል፤ ይህ ሥራ እንዲሳካ ላደረጉት ትዕግስታቸው፤ የለገሱኝን ጠቃሚ ሃሳቦቻቸውና ትብብራቸውን አመሰግናለሁ።

አላህም የስኬት ወሳኝና ባለቤት ነው፤

ደራሲው !!!

## ስለዚህ ተከታታይ መልዕክት ገለፃ

ይህ ተከታታይ ምናባዊ ወይም ምሳሌያዊ ታሪክ የተዘጋጀው፤ የሙስሊም ቤተሰብ ሕይወት በተለይ ልጆቻቸው፤ በትምህርት ቤት፤ በመስጊድና በማሕበራዊ ሚዲያ እና ካካባቢያቸው ፀባይ ጋር እንዲግባቡ ለማድረግ ታቅዶ ነው። ይህም ተከታታይ መልእክት፤ ለሙስሊም አማኝ ቤተሰብና የቤተሰብ አባል፤ ወቅታዊ የሆኑ በአላህ መኖር እምነትና ክህደት ዙሪያ፤ የሚገጥማቸው ችግር እንዴት መጋፈጥ እንዳለባቸው እና በቤተሰብ መካከል በእምነትና በክህደት ዙሪያ ውይይት በማድረግ፤ በልብ ውስጥ እምነትን ለመትከልና ወጣቶችን ከክህደት ለመከላከል ሲሆን፤ በተጨማሪ ይህ መልእክት በትምህርት ቤትም ሆነ በሌላ ቦታ፤ በማሕበራዊ ሕይወት ውስጥ ያሉትን ክስተቶችን በመቃኘት ያጠነጥናል።

ይህም ተከታታይ መልዕክት የተዘጋጀበት ዋና አላማ፤ በተማሪዎች ላይ በቀጥተኛው ሃይማኖት በኢስላም ዙሪያ ጤናማ የሆነ አመለካከት ለማስረፅና፤ አስተማሪም እንዳስፈላጊነቱ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ለአስተማሪዎች ተጨማሪና አጋዥ እንዲሆን፤ ጥራት የተገባው ፈጣሪያችን ብቸኛ ተመላኪው አላህ ለመኖሩ በኢስላም ሸሪዓዊ ሕግና በዕውቀት ላይ የተመሰረተ መረጃንም ለማቅረብ፤ በተጨማሪ ለአቅመ አዳም የደረሱ ወጣት ሙስሊሞችም ሆነ በእድሜ ከዚያ በላይ ላሉ ሙስሊሞች በሙሉ፤ በረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በኩል ከአላህ የመጣውን ኢስላማዊ መልዕክት ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ፤ ቀለል ባሉ በቤተሰባዊ ውይይቶች መልክ በማቅረብ፤ በየቀኑ በሚያሳልፉት የሕይወት ተሞክሮ በትምህርት ቤት፤ በመስጊድ ወይንም በመጫወቻ ቦታዎች፤ እና ከውጭው ዓለም ጋር በሚያደርጉት የበይነመረብ ግንኙነቶችና በዘመናዊ የመገናኛ ብዙሃን በሚገጥማቸው ክስተቶች ዙሪያ መመካከር አስፈላጊ እንደሆነ በዚህ ፁሑፍ ይንፀባረቃል። የዚህ መልእክት ሌላው አላማ፤ ለአባቶችና ለእናቶች የቁርአን መልእክት ትክክለኛነት መሠረታዊ በሆኑ መረጃዎችና ብቁ በሆኑ ምልከታዎች በማስገንዘብ፤ በገበታ ወቅትም ሆነ በሌሎች ዝግጅቶች ላይ፤ እውቀትን ለማንሸራሸርና በልጆቻቸው አስተሳሰብ ላይ ሐቅን ለማስረፅ፤ በአምላክ የለሽነት አስተሳሰብ እንዳይበከሉ፤ ክህደትን ተቃዋሚ ሆነው እንዲፀኑና እንዲጠበቁ መሠረታዊ በሆኑ በኢስላም ሕግጋት ላይ ከጥርጣሬ ነፃ ለማድረግ ታቅዶ ነው። በመጨረሻም በዚህ ቀለል ባለ የዕውቀት ርእሰ ጉዳይ፤ በቂ በሆነ መረጃ የታገዘና የአቀራረብ ስልቱም በአማረ መልኩ በመሆኑ፤ ለሁሉም ሐቅንና መልካም ሥነ–ምግባርን ለሚፈልግ ሁሉ ምናልባት (የአላህ ፈቃዱ ከሆነ) ይጠቅም ይሆናል፤ ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ምስጋና ይገባው።



# የመጀመርያው ሸንጎ

የማሊክ አባት፡- አሰላም አለይኩም የማሊክ እናት፤

የማሊክ እናት፡- ወአለይኩም ሰላም ወረሕመቱላህ፤ ሁኔታህ እንዴት ነው? የማሊክ አባት፤ ዛሬ ጠዋት የወሰድከው መድሐኒት ጠቅሞሃልን?

የማሊክ አባት፡- አልሐምዱ ሊላህ፤ በጤናዬ ላይ የተወሰነ መሻሻል ይሰማኛል፤ ለዚህም ነው ከጀምዓ ጋር ተገኝቼ የፈጅር ሰላት ለመስገድ ወደ መስጊድ ለመሄድ የተደፋፈርኩት፤

የማሊክ እናት፡- ምንም ችግር የለም፤ የአላህ ፈቃዱ ከሆነ (ሕመምህ ወንጀልህን) የሚያፀዳ ይሁን፤ ፈጣን ፈውስ እንድታገኝና ከመጥፎ ሁሉ እንዲጠብቅህ አላህን እለምንልሃለሁ፤

የማሊክ አባት፡- አሚን፤ ዱዓሽ ያረካኛል፤ ወደ ልቤ ውስጥ ደስታን ነው የሚያስገባው፤ በነገራችን ላይ የመስጊዳችን ኢማም ሼኽ ሙዓዝ ዛሬ ጠዋት ከፈጅር ሰላት በኋላ የፊታችን እሮብ በመስጊድ ውስጥ የኩሱፍ ሰላት እንደሚሰግዱ አስታውቀዋል፤ እኔም ከነርሱ ጋር ይህንን ሰላት ለመስገድ በጥሩ የጤና ሁኔታ ላይ እንድሆን እመኛለሁ፤

የማሊክ እናት፡- በርግጥ ይህ ዜና ትክክል ነው፤ በዓረብ ሃገሮችና በሌሎችም የዓለም ሃገሮች ላይ፤ የፊታችን እሮብ ሙሉ ለሙሉ ኩሱፍ እንደሚከሰት በዜና አስታውቀዋል፤ ነገር ግን የማሊክ አባት ንገረኝ እስኪ፤ በኢስላም የኩሱፍ ብያኔ ምንድነው? ሰላቱስ በሁሉም ሙስሊም ላይ ግዴታ ነው የሚሆነው?

አቡ ማሊክ፡- አይደለም እኔ የማውቀው ሱና ሙአከዳ መሆኑን ነው፤ የሰላቱም ተግባር የሚከናወነው ፀሐይ በጨረቃ ስትጋረድ (ኩሱፉ አል ሸምስ) ሲከሰት ወይንም ጨረቃ በመሬትና በፀሐይ መሐከል ገብታ በመሬት ስትጋረድ (ኹሱፍ አል ቀመር) ወቅት ጊዜ ብቻ ነው፤ ሰላቷን የሰገዳት ምንዳውን ያገኛል፤ ሰላቱ ያመለጠው ምንም ወንጀል የለበትም። በዚህ ዓለም ውስጥ የአላህ ተዓምር በጣም ብዙ ነው፤ ይህም የፀሐይ ግርዶሽ አንዱ ነው።

ኡሙ ማሊክ ፡- በርግጥ ልጆች ከትምህርት ቤት የሚወጡበት ጊዜ ደርሶዋል፤ ልጆቹን ለማምጣት አንተ ትሄዳለህ? ወይንስ ልጆቹን ለማምጣት እኔ ልውጣ?

አቡ ማሊክ፡- ችግር የለም ልጆቹን ለማምጣት እኔ እሄዳለሁ፤ እባክሽን የመኪናውን ቁልፍ አቀብይኝ።

ኡሙ ማሊክ፡- ተቀበል ቁልፉን ሰላም ከአንተ ጋር ይሁን።



## ሁለተኛው ሸንጎ

ማሊክና መርየም፡- አሰላም አለይኩም አባቴ ሆይ።

አቡ ማሊክ፡- ወአለይኩም ሰላም ወረሕመቱላሂ፤ እንዴት ናችሁ ውዶቼ ሆይ፤ የዛሬውን የትምህርት ቤት ውሎ እንዴት አሳለፋችሁት?

ማሊክ፡- አባቴ ሆይ ዛሬ በጣም ድንቅ ቀን ነበር፤ የመረብ ኳስ ግጥሚያ ላይ ተሳትፌ ነበር፤ ቡድናችንም በጥሩ ውጤት አሸንፎዋል፤ አልሃምዱ ሊላህ።

አቡ ማሊክ፡- በጣም ሸጋ ነው፤ መርየም ሆይ ዛሬ ምን ተማርሽ።

መርየም፡- በዛሬው ቀን በጣም ጥሩ ነገር ነው የተማርኩት፤ እርሱም ስለፀሐይ ግርዶሽ (ኩሱፍ አልሽምስ) እና ስለጨረቃ ግርዶሽ (ኹሱፍ አል ቀመር) ነው፤ የሳይንስ አስተማሪያችንም ስለዚህ ጉዳይ በዝርዝር አስተምራናለች፤ የቁርአንና የእስላማዊ ትምህርቶች አስተማሪያችንም፤ ኡስታዛ ዘይነብም ስለ የኩሱፍ ሰላት ሥርዓቱን አስተምራናለች፤ ከረሱል (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ልጆች አንዱ ስለሆነው፤ በጨቅላነቱ ስለሞተው ስለ ኢብራሂም ታሪኩን አወሳችልን፤ የኢብራሂም ሞት ቀንም ከፀሐይ ግርዶሽ ቀን ጋር ገጥሞ ነበር።

አቡ ማሊክ፡- አዎን የኢብራሂም ሞት፤ በዚያ በፀሐይ ግርዶሽ ቀን መሆኑ በሁሉም ዘንድ የታወቀ ነው።

መርየም፡- የቁርአን አስተማሪያችንም እንደነገረችን ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በልጃቸው ኢብራሂም ሞት አዝነው አይናቸው እንባ አነባ፤ ነገር ግን በትእግስት ፅኑ፤ የአላህንም ፍርድና ውሳኔ ያልተቃወሙ ሆነው እንዲህም እንዳሉ አወሳችልን፤ (አይን ያነባል ልብም ያዝናል፤ ጌታችንም የሚወደውን በስተቀር ሌላ ምንም አንልም፤ ኢብራሂም ሆይ ስለተለየኸን በጣም አዝነናል) አሉ።


አቡ ማሊክ፡- አልኸምዱ ሊላህ እኔም ወደዚህ ኢስላማዊ ትምህርት ቤት ያመጣኋችሁ፤ እንደዚህ አይነቱን ነገር እንድትማሩ ነው፤ በጣም የገረመኝ ጉዳይ ደግሞ የተፈጥሮ ሳይንስ አስተማሪና የኢስላማዊ ትምህርቶች አስተማሪ፤ በመካከላቸው መናበብ መኖሩንና ተማሪዎችም በሁሉም እውቀት ዙሪያ የተሟላ ብቃት እንዲኖራቸው መደረጉ ነው።

ማሊክ፡- አስተማሪያችን ኡስታዝ ሐሰንም እንደዚሁ ስለዚህ ጉዳይ ባጭሩ ተናግሮዋል።

አቡ ማሊክ፡- የፊታችን እሮብ ስለሚከሰተው የፀሐይ ግርዶሽ በዜናው ሁሉም መወጠር ጀምሮዋል።

መርየም፡- አልሃምዱ ሊላህ ቤታችን ደረስን፤ በመኪናዎች ብዛት ሰበብ መንገዱ ተጨናንቆ ነበር፤ ነገር ግን ከውዱ አባታችን ጋር ድንቅ ወሬ በመያዛችን፤ የመንገዱ እርቀት ምንም አልተሰማንም።

አቡ ማሊክ፡- አመሰግናለሁ ልጄ መርየም፤ በዚህ ትምህርት ቤት የምትማሩት እንዲጠቅማችሁ አላህን እለምነዋለሁ።



## ሶሥተኛ ሸንጎ

ኡሙ ማሊክ፡- እንኳን ሰላም መጣችሁ፤ ሕፃናት ልጆቼ ሆይ፤ እንዴት ናችሁ?

ማሊክና መርየም፡- እናታችን ሆይ አሰላም አለይኩም።

ኡሙ ማሊክ፡- ወአለይኩም ሰላም ወረሕመቱላሂ።

ማሊክ፡- እኔ ከእንግዲህ ሕፃን ልጅ አይደለሁም፤ እናቴ ሆይ፤ እኔ እድሜዬ አሥራ ሁለት አመት አልፎዋል፤ በሁሉም ዝግጅት ላይ፤ በእጅ መረብ ኳስ ከቡድኑ ጋር የሚያሸንፍ ኮማንዶ ወጣት ሆኛለሁ።

አቡ ማሊክ፡- ማሊክ ሆይ እርሱ በመሰረቱ ጨዋታ ብቻ ነው፤ ልጄ ሆይ አታጋንን፤ ጨዋታ መሆን ያለበት የአካል ብቃትን ለማስተካከልና ለጤና ብቻ ነው።

መርየም፡- ማሊክ ጨዋታውን በማሸነፋችሁ በፍሊስጢን አቅሳ መስጊድን ነፃ ታወጣላችሁ፤ ወይንስ የኢስላምንና የሙስሊሞችን ክብር ታስመልሳላችሁ።

ማሊክ፡- በመጨረሻ (መርየም) የዘመናችን ፈላስፊት፤ የዘመኗ ጠበብት፤ የሰውና የጋኔን ሙፍቲ ተናገረች።

ኡሙ ማሊክ፡- እየሳቀች ማሊክ ሆይ እንዲህ አይነት መልስ ከየት ነው የምታመጣው።

ማሊክ፡- እናቴ ሆይ እኔ ከእንግዲህ ወደ ሕፃንነት አልመለስም፤ እ .... ትልቅ ሆኛለህ አላልኳችህምን።

ኡሙ ማሊክ፡- የማሊክን ንግግር እያቋረጠች፤ እንዲያውም እድሜህ ስልሳ አመት ቢሞላም ልጄ ሕፃኔ እንደሆንክ ነው የምትቀረው፤ የዚህ (የወላጅነት) ትርጉም አድገህ ልጆች ሲኖርህ ካልሆነ በስተቀር አሁን አይገባህም፤ አድገህ የልጆች አባት ስትሆን ያለህን ስሜት ትነግረኛለህ።

አቡ ማሊክ፡- ኡሙ ማሊክ እውነት ተናግረሻል፤ የዚህ የወላጅነት ስሜትን ከአባቶችና ከእናቶች በስተቀር ማንም አይረዳውም፤ ስለዚህም ነው (ነብዩ ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለ) በልጃቸው በኢብራሂም ሞት ያለቀሱት፤ በረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ማልቀስ ከፊል ሰሃባዎች (ረዲየላሁ ዓንሁም) ተገረሙ፤ ከነርሱም ውስጥ አብዱረሕማን ቢን ዓውፍ (ረዲየላሁ ዓንሁ) እንደዚህ አለ፤ (አንተም ረሱል ሆይ ታለቅሳለህን) ሲል፤ ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (የዓውፍ ልጅ ሆይ እርሷ (ማንባት) እዝነት ናት) አሉት። አብዱረህማን ኢብኑ ዓውፍ (ረዲየላሁ ዓንሁ) በፊት ሙስሊም በሞት ምክንያት ወዳጅ ሲለየው ማልቀስ (ማንባት) አይፈቀድለትም ብሎ ይገምት ነበር፤ ለዚህም ነው በረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በማንባት ተግባር የተገረመው፤ ወዳጁም ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንደገለፁለት፤ (ይህ እንባ የእዝነትና የመሳሳት እንባ ነው፤ እንጂ በአላህ ውሳኔ ላይ መቃወም አይደለም) አሉት።

ኡሙ ማሊክ፡- ወዳጃችን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በሁሉም ነገር ላይ መሪያችን ነበሩ፤ በነገራችን ላይ አቡ ማሊክ ሆይ! ልጆችን ከትምህርት ቤት ለማምጣት በሄድክበት በሼኾቹ በአንዱ በዩቱዩብ መድረክ ላይ፤ በነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ዘመን ስለተከሰተው የፀሐይ ግርዶሽ ታሪክ ሲያወሳ፤ ከዚህ በፊት ምንም ትኩረት ስለማልሰጠው ጉዳይ ነው የሰማሁት።

አቡ ማሊክ፡- ኡሙ ማሊክ ሆይ ሼኹ ምንድን ነው ያለው?

ኡሙ ማሊክ፡- በዚያች በሼኹ  ሙሃደራ በጣም የገረመኝ፤ ሼኹ እንዳለው በርግጥ የኢብራሂም ሞት የፀሐይ ግርዶሽ ቀን መሆኑ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ትክክለኛ ነብይ ለመሆናቸው ጠንካራ መረጃ ነበር፤ ነገር ግን እርሳቸው ውሸታምም ሆነ ነብይነታቸውን ለይስሙላ ያደረጉ ሰው አልነበሩም።

መርየም፡- ሼኹ እንዲህ አይነት የጥናት ምርምር ላይ እንዴት ደረሱ?

አቡ ማሊክ፡- ልክ ነው እንደዚህ አይነት ጥሩ ትርጉም ላይ ተመራምሮ እንዴት ደረሰ?

ኡሙ ማሊክ፡- ሼኹ እንዳለው፤ ከፊል ሙስሊሞች ያችን ቀን ፀሐይ የተጋረደችው በኢብራሂም ሞት ነው ብለው ገምተው ነበር፤ ምክንያቱም ከነብያቶች ውስጥ የአንዱ ነብይ ልጅ ነውና። ነገር ግን ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ይህንን የተሳሳተ ግምት ለማስተባበልና የተሳሳተውንም አረዳድ ለማስተካከል ተቻኮሉ፤ ምንም ትርጉሙ በማያሻማ መልኩ በግልፅ አብራሩት።


ማሊክ፡- ለማለት የፈለግሽው ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የፀሐይ ግርዶሹ ከኢብራሂም ሞት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ያሉትን ነው?

ኡሙ ማሊክ፡- ሼኹ አላህ ምንዳውን ይክፈለውና በጉዳዩ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥቶዋል፤ሼኹም እንዳለው፤ የውሸታሞች ፀባይ ነብይ ነኝ፤ ተአምር አለኝ፤ የተፈጥሮን ሂደት የጣሰ ነገር እፈጥራለሁ፤ የሚሉ አጭበርባሪዎች በሰው ፊት ውሸታቸውን የሚያጠናክር ማንኛውንም አይነት ቅጥፈት ይፈልጋሉ ። ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም ግን ሐሰተኛ ነብይ ቢሆኑ የፀሐይ ግርዶሹን ክስተት ከርሳቸው ሃዘን ጋር መግጠሙን በመጠቀም የሚቃወሟቸውን ሰዎች ፀጥ ባሰኟቸው ነበር፤ ወይንም የፀሐይዋ ግርዶሽ ከእኔ ሐዘን ጋር የገጠመ ነው በማለት፤ ሰዎች የነብይነታቸውን እምነት እንዲያጠናክር በተጠቀሙበት ነበር።

አቡ ማሊክ፡- ይህ በጣም ድንቅ ምርምራዊ ትንታኔ ነው ዳዕዋ የሚያደርጉት ሼኽ የሰጡት፤ አንደኛ በርግጥ ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ትክክለኛ መልክተኛ ናቸው፤ ሁለተኛ እርሳቸው ነብይነታቸውን ለሰዎች ለማረጋገጥ ሐሰት የሆነ መረጃ አያስፈልጋቸውም።

ኡሙ ማሊክ ፡- በትክክል ሼኹም ይህንኑ ሃሳብ ነው ለማስተላለፍ የፈለገው።

አቡ ማሊክ፡- የአላህ ፈቃዱ ከሆነ የፊታችን እሮብ እለት ከኩሱፍ ሰላት በኋላ፤ ይህንን መልካም ምሳሌ እንዲያመላክቱ ለመስጊዳችን ኢማም አስታውሰዋለሁ፤ በዚህን ጊዜ ወጣቶች እንደዚህ አይነት ግልፅ መረጃ በጣም ያስፈልጋቸዋል።


یا اللہ
جل جلالک

## አራተኛው ሸንጎ

አቡ ማሊክ፡- አሰላም ዓለይኩም ሼኻችን።

ሼኽ ሙዓዝ፡- ወአለይኩም ሰላም ወረሕመቱላሂ ወበረካቱሁ እንደምን አላችሁ።

አቡ ማሊክና ማሊክ፡- አልሃምዱ ሊላህ እኛ ሰላም ነን።

አቡ ማሊክ፡- ኢማም ሆይ የፊታችን እሮብ የሚሰገደውን የሰላት አል ኩሱፍ በተመለከተ የምናናግራችሁ ነገር አለ ልትፈቅድልን ትችላላችሁ?

ሼኽ ሙዓዝ፡- አንተ ዘንድ ያለውን ነገር አምጣ (ተናገር) ተፈቅዶልሃል።

አቡ ማሊክ፡- በነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ዘመን፤ በተከሰተው ኩሱፍ ዙሪያ ባለቤቴ ኡሙ ማሊክ በዩቱዩብ መድረክ ዳዕዋ ከሚያደርጉት መሐል አንዱ ሼኽ፤ በዚህ በኩሱፍ ዙሪያ ሲያብራራ በሰማች ጊዜ በጉዳዩ በቤተሰባችን አባላት መካከል በተደረገው ውይይት የነብዩን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ነብይነት የሚያረጋግጥ ትልቅ ጥቅምና መረጃ ተገንዝበናል።

ሼኽ ሙዓዝ፡- ጉዳዩ በርግጥ ትልቅ ነው፤ ምንድን ነው ይህ ጥቅም?

አቡ ማሊክ፡- በዩቱብ ዳዕዋ የሚያደርገው ሼኽ እንዳስታወሰው፤ ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዲህ ብለዋል፡- (በርግጥ ፀሐይና ጨረቃ ከአላህ ተአምራቶች ውስጥ የተወሰኑ ተአምር ናቸው፤ ለማንም ሞትም ሆነ ሕይወት ሲሉ አይጋረዱም) አሉ። በዚህም ንግግራቸው ትክክለኛ ነብይነታቸውን ያረጋገጡበት አጋጣሚ ነው።

ሼኽ ሙዓዝ፡- ሱብሃን አላህ በጣም ያማረ ትውስታ ነው፤ ይህንን ታሪክ ምንም እንኳን ደጋግሜ ባነበውም እንደዚህ አይነት ጥቅም እንዳለበት አላስተዋልኩም፤ በጣም ግልፅ ነው ወዳጃችን (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ሰዎች እንደሚሉት በፀሐይ ግርዶሽ ቀን ፀሐይ የተጋረደችው ልጃቸው ኢብራሂም ስለሞተ ነው በማለታቸው፤ አጋጣሚውን ተጠቅመው ነብይነቴን አረጋግጡልኝ አላሉም፤ የሐሰት ነብይ ቢሆኑ ሰዎችን ለማሳመን ይህ ጥሩ አጋጣሚ ነበር፤ እሳቸው ግን አላደረጉትም።

አቡ ማሊክ፡- የረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሕይወት በጠቅላላ፤ አርዓያና ትልቅ ትምሕርት ነው።

አቡ ማሊክ፡- ንግግሩን በመቀጠል፤ ሼኽ ሆይ ይህን ጥቅም ያዘለ መልእክት ከኩሱፍ ሰላት በኋላ ምናልባት ለሰዎች እንድታስታውሳቸው ፈልጌ ነበር አለ።

ሼኽ ሙዓዝ፡- አቡ ማሊክ ሆይ ምንዳችሁን አላህ ይክፈላችሁ፤ እናንተ ምንግዜም ቢሆን ወደ መልካም ተግባር ቀዳሚዎች ናችሁ፤ የአላህ ፈቃዱ ከሆነ አደርገዋለሁ፤ እዚሁ ታሪክ ላይ ሌላ ጠቃሚ ታሪክ አለ እርሱም በርግጥ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ልጃቸውን ኢብራሂም በሞት አደጋ በማጣታቸው በሃዘን አልተወጠሩም፤ ዋና

ግዴታቸው ሰዎችን ማስተማር ነው፤ የ(ቁርአን) መልክት አድራሽ ለመሆናቸው ይህ መረጃ ነው፤ የአደጋውም ሆነ የክስተቱ አይነት በጣም ቢገዝፍም ምንም ሳይዛነፍና ሳይቀንስ መለኮታዊ መልእክታቸውን ከማድረስና ግዴታቸውንም ከመወጣት አይዘናጉም። በምንናገረውና በምንሰማው እንድንጠቀም አላህን እለምነዋለሁ።

አቡ ማሊክ፡- በትህትና ተመስጠው፤ ይህንንም ሃሳቤን በመልካም በመቀበላችሁ አላህ ምንዳውን ይክፈላችሁ።

ሼኽ ሙዓዝ፡- የማሊክ አባት ሆይ! ግዴታን በመወጣት ላይ ምስጋና አይኖርም፤ አንዳችን አንዳችንን የሚያጠናክር አንድ እጅ መሆን አለብን፤ ይህንንም የኢስላም ሃይማኖት ለማገልገልና በድል እንዲወጣ ለማድረግ ሁላችንም መመካከር አለብን።

አቡ ማሊክ፡- ለጥረትህ አላህ በረካ ያድርግህ በርግጥ ይህ መተባበር በዚህን ወቅት ሙስሊሞች ማድረግ የሚገባቸው ተግባር ነው።

ማሊክ፡- የአላህ ፈቃዱ ከሆነ እኔም የዚህን ታሪክ ጥቅም ለትምህርት ቤት ጓደኞቼ አስታውሳቸዋለሁ።

ሼኽ ሙዓዝ፡- ማሊክ ሆይ አላህ በረካ ያድርግህ፤ ትንሹ ዳዕዋ አድራጊ ብለን ሥም እናወጣልሃለን፤ ያንተንም መሰል አላህ ያብዛው፤ ሁሉም ቦታ ላይ የሙስሊም ልጆችን አላህ ያስተካክል።

አቡ ማሊክ፡- አሚን!

## በትምህርት ቤት ውስጥ የትምህርቱ አጠቃቀም

1 ይህንን ተከታታይ ውይይት ለከፍተኛ ደረጃ ክፍል፤ ለጀማሪዎችና ለመካከለኛ ደረጃ ክፍል፤ በአረብኛ ቋንቋ የንባብ ክፍለ ጊዜ አስተማሪው ሊጠቀምበት ይችላል። ከዚያም በታሪኩ ውስጥ የተካተቱትን ሁሉንም ትርጉም፤ ተማሪዎች ስለመረዳታቸውና ስለመገንዘባቸው ችሎታቸው ይፈተናል፤ ከዚያም መልእክቱ የአረብኛን ቋንቋ ትምህርትንና ወደ አላህ መንገድ ጥሪን ያጠቃልላል።

2 ይህንንም መልእክት የኢስላማዊ ትምህርት አስተማሪ ለወንድና ለሴት አስተማሪዎች፤ እውቀታቸው እንዲጨምር ታዋቂ በሆኑ የማሕበራዊ በይነ መረብ መገናኛዎች አማካኝነት፤ የኢስላም መልእክት ሰላማዊና አዎንታዊ መሆኑን አውቀው እንዲረጋጉና እምነታቸውም እንዲጨምር፤ የኢስላማዊ ትምህርቶች አስተማሪ ይጠቀምበታል።

3 ኢስላማዊ መልክቶችን በድራማ መልክ ለሚያስተላልፉ፤ ተሰጥዖ ያላቸው ሙስሊሞች፤ ዓላማውን የእምነት ጉዳይን ኢስላምን የሚያገለግልና የዘመኑን ተግዳሮቶች በመጋፈጥ የሚያስተካክል፤ አጭር ቲያትሮችን በማዘጋጀት፤ አስተማሪው ይህንን መልእክት ሊጠቀምበት ይችላል።

4 ይህንንም መልእክት አባቶችና እናቶች፤ ልጆቻቸውን ንባብ በሚያለማምዱበት የንባብ ክፍለ ጊዜ፤ በመገልገል በታሪኩ ውስጥ ባለው አስፈላጊ መልእክት ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

በመጨረሻም፡-

አንባቢ ተማሪ በእያንዳንዱ ታሪክ መጨረሻ ላይ በታሪኩ ዙሪያ ዋና አላማውና የታሪኩንም ጥቅም በአጭሩ ጠቅለል አድርጎ ማቅረብ ይጠበቅበታል። በዚህ ማጠቃለያ ላይ የትምህርቱን ትግል በአሸናፊነት ለመወጣትና በተሻለ መልኩ መረዳትን ለማስተካከል የግድ ልዩ ትኩረት መሰጠት አለበት።

## በጣም አስፈላጊ ማሳሰቢያ

ይህ ተከታታይ መልእክት፤ በሩቅም ሆነ በቅርብ የቤተሰብ ግንኙነት፤ የግድ በቁም ነገር ላይ ብቻ የተወሰነ ነው ብሎ ማሰብ፤ ወይም ሁልግዜ የቤተሰብ ውይይት ላይ የሃሳብ ክርክር ወይንም በዚህ ባሳለፍነው አይነት ታሪክ ላይ፤ በዕውቀት ዙሪያ ላይ ብቻ የተገደበ መሆን የለበትም፤ የቤተሰብ ግንኙነት በሁሉም የሰው ልጅ የሕይወት ገፅታዎች ላይ የሚያጠነጥን መሆን አለበት፤ ለምሳሌ የቤተሰብ ግንኙነት ትብብርን፤ መዋደድን፤ መተዛዘንን፤ እስፖርታዊ ውድድሮችን፤ የቤተሰብ ሕይወትን የሚያዝናና ጨዋታን፤ ችላ የሚል መሆን የለበትም፤ ስለዚህ ዋና የሚያስፈልገው የሙስሊም ቤተሰብ ሕይወት በሁሉም ዙሪያ ሚዛናዊ መሆን አለበት።

### በዚህ ታሪክ ውስጥ አንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ጥቅሙ

### አንደኛ ደረጃ ወይም ዋና ጥቅሙ፡-

የነብዩ መሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ልጅ ኢብራሂም የሞተ ቀን፤ የተከሰተው የፀሐይ ግርዶሽ (ኩሱፍ) ትእይንት ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ትክክለኛ ነብይ ለመሆናቸው ከተወሳው ታሪክ ማረጋገጥ ይቻላል።

### ሁለተኛው ጥቅም፡-

- ወላጆች ልጆቻቸው በትምህርት ቤትም ሆነ በመስጊድ በሚማሩት ትምህርት ላይ፤ ትኩረት መስጠታቸው በጣም አስፈላጊ ነው።
- በቤተሰብ ሸንጎ ላይ ውይይቱን፤ በሚያገለግሉና በሚጠቅሙ ጉዳዮች ዙሪያ ማሳለፍ።
- የሙስሊም ቤተሰብ በአላህ ፈጣሪነትና በብቸኛ ተመላኪነቱ ለማመን፤ እና ነብዩ መሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ትክክለኛ ነብይ መሆናቸውን እምነቱን ለማጠናከር፤ የተፈጥሮ ልዩ ክስተቶች በሚከሰቱበት ጊዜ (ከኢስላም ጋር ተያያዥ የሆኑ) አዎንታዊ የሆነን ግምት ለመውሰድ ያገለግላል።
- የኢማሞች፤ ዳኢዎች፤ ሼኮችና የሃይማኖት መሪዎች፤ ወደ ሰዎች በተለይ ወደ ሕፃናት ተናንሰው በመልካም ፀባይ መቅረብ እንዳለባቸው ያስገነዝበናል።
- የሙስሊም ትምህርት ቤት ውስጥ፤ ተማሪው በእምነቱ እንዲጠናከርና በስብእናውም የተሟላ እንዲሆን፤ የዘመናዊ የቀለም ትምህርት አስተማሪና የኢስላም ሃይማኖት አስተማሪ መካከል መልካም ግንኙነት ፈጥረው ተናበው መሥራት እንደሚገባቸው ያስገነዝበናል።
- ዋናው ጥብቅ ጉዳይ በሙስሊም ሕብረተሰብ ውስጥ ሦስት ቤቶችን የሚያገለግሉ ሰዎች በጣም መተባበር ይገባቸዋል፤ እነዚህም ሦስት ቤቶች የሚከተሉት ናቸው ፡- ▪ መስጊድ የአላህ ቤት፤
  ▪ ትምህርት ቤት የዕውቀትና የመማሪያ ቤት፤ ▪ መኖሪያ ቤት የቤተሰብ ቤት ናቸው።

ፈጣሪን የሚክዱትን በጋራ እንከላከል

معاً ضد الإلحاد

ድርሰት: ሐሰን ሺባኒ ትርጉም ሰይፈዲን አበሻ ያሲን

تأليف: حسن شبّاني

ይህ ከተከታታይ መልእክቶች አንዱ የሆነው መልእክት፤ የሙስሊም አማኝ ቤተሰብን ሕይወት፤ በገሃድ ከሚታየው ከዘመናዊ ሕይወት ጋር ለማጣጣም፤ ከቁርአን ከሱናና ከነብያዊ ታሪክ እውነታዎች ጋር በማዛመድ፤ የተለያዩ በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚታዩትን ክስተቶች፤ በእምነታዊ አረዳድ ተረድቶ፤ በሕዝበ ሙስሊሙ በልቡ እንዲሰርፅ በማድረግ፤ የሚጠቅም መልእክት ነው።

በምሳሌነት የቀረቡት እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል፤ በዙሪያቸው ያሉት ሰዎች የሚገጥማቸውን ክስተቶች ሁሉ፤ ከፊል ኢስላማዊ መረጃዎችንና የነብያዊ ታሪኮች ጋር በማገናዘብ፤ የነብዩ መሐመድን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ትክክለኛ ነብይነትን ለማስረዳት ይሞክራሉ።

ይህም የሚያቀርቡት ኢስላማዊ መረጃ፤ ኹጥባ አድራጊዎች፤ መካሪዎችና አስተማሪዎች፤ ትኩረት የማይሰጧቸውን ነጥቦችን ነው፤ ይኸውም መረጃቸው የቁርአን መልእክት ትክክለኛነትና የኢስላም መልእክት ሐቀኛነት፤ ከማጭበርበርና ከሐሰት የራቀ ለመሆኑ ጠንካራ መረጃ ነው፤ መረጃውም ታዳጊ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች በኢስላም ሃይማኖት ላይ የእምነት መጠናቸው እንዲጨምር አስተዋፅዖ ያደርጋል፤ ፈጣሪን ከመካድ በሽታና የነብዩ መሐመድን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) መልእክትን ከመጠራጠርም ይከላከልላቸዋል።

ደራሲው:-

من عناوين السلسلة:

- "هذه الثمرة ليست لنا"
(علمنا أحكام الزكاة يا أستاذ)

- "لست في حاجة إلى حراسة البشر"
(و الله يعصمك من الناس)

Itkan Kitap
إتقان للنشر

05515897390
itkankitapevi
WWW.itkanpublishers.com

ISBN 978-625-76294-3-0